የነብዩላህ ኢብራሂም ታሪክ

ካንተ በፊትም መልክተኞችን በእርግጥ ልከናል። ከእነርሱ ባንተ ላይ የተረክንልህ አልሰ። ከእነርሱም ባንተ ላይ ያልተረክነው አልሰ።

[ሱረቱ ኸል-ሙእሚን - 78]

[የነብዩላሂ ኢብራሂም ታሪክ ቁርኣን ላይ ቱክረት ከተሰጣቸው የነብያት ታሪክ ውስጥ በግንባር ቀደምትነት ይመደባል። ታሪካቸው ቁርኣን ውስጥ በ17 ምእራፍ ወደ 69 ጊዜ ተጠቅሷል። ይህ የሚያሳየው ታሪካቸው ምን ያክል አስፈላጊና ቁም ነገር አዘል መሆኑ ነው።]

በኡስታዝ አቡ ዑበይዳህ ባህሩ ተካ በተከታታይ በቴሌግራም ቻናል ቀርቦ በወንድም አቡ ዒምራን ሙሐመድ መኮንን በሰኔ 2016 ዓ.ር በpdf መልኩ ለአንባቢያን ምቹ ሆኖ ቀረበ ።

የነብዩላሂ ኢብራሂም ታሪክ

- የነብዩላሂ ኢብራሂም ታሪክ ቁርኣን ላይ ቱክረት ከተሰጣቸው የነብያት ታሪክ ውስጥ በግንባር ቀደምትነት ይመደባል። ታሪካቸው ቁርኣን ውስጥ በ17 ምእራፍ ወደ 69 ጊዜ ተጠቅሷል። ይህ የሚያሳየው ታሪካቸው ምን ያክል አስፈላጊና ቁም ነገር አዘል መሆኑ ነው።

- **ነብዩላሂ ኢብራሂም ዒራቅ ውስጥ ባቢል በሚባል ቦታ በጣኦት አምላኪ ማህበረሰብ ውስጥ ተወለዱ። ከህብረተሰቡ ውስጥ ኮከብ የሚያመልክ፣ ጨረቃ የሚያመልክና ፀሀይ የሚያመልክ እንዲሁም ከእንጨት የተሰራ ጣኦት የሚያመልክ ነበር። አባታቸው ኣዘር ከእንጨት ጣኦት እየሰራ ይሸጥ ነበር። እሳቸው በልጅነታቸው እርሻ ይሰሩ ነበር። አባታቸው ጣኦት እያዞሩ እንዲሸጡላቸው ሲያዙዋቸው ተቀብለው መሬት ለመሬት እየጎተቱ የማይጠቅምና የማይጎዳ የሚገዛ እያሉ ያዞሩ ነበር። በዚህም ምክንያት ማንም የሚገዛ ስለማያገኙ ይዘውት ይመለሳሉ።**

- እድሜያቸው 13 አመት ሲሞላቸው ፈጣሪዬ ማን ነው ብለው ማሰብ ጀመሩ። ቤተሰቦቻቸውና ማህበረሰቡ በሚያመልኩት ነገር ደስተኛ አልነበሩም። ለብቻቸው ሲሆኑ ማን ነው የፈጠረኝ እያሉ ይብሰለሰላሉ።

⇨ በዚህ ሰሜት ውስጥ ሆነው ከቤት ወጥተው ወደ ሰማይ በሚያዩበት ጊዜ የተከሰተውን አላህ ሲነግረን በአል አንዓም ምእራፍ ከ75 – 79 ድረስ እንዲህ ይለናል:–

وَكَذَٰلِكَ نُرِي إِبْرَاهِيمَ مَلَكُوتَ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ وَلِيَكُونَ مِنَ الْمُوقِنِينَ

እንደዚሁም ኢብራሂምን (እንዲያውቅና) ከአረጋጋጮቹም ይኾን ዘንድ የሰማያትንና የምድርን መለኮት አሳየነው።።

فَلَمَّا جَنَّ عَلَيْهِ اللَّيْلُ رَأَىٰ كَوْكَبًا ۖ قَالَ هَٰذَا رَبِّي ۖ فَلَمَّا أَفَلَ قَالَ لَا أُحِبُّ الْآفِلِينَ

ሌሊቱም በእርሱ ላይ ባጨለመ ጊዜ ኮከብን አየ። «ይህ ጌታዬ ነው» አለ። በጠለቀም ጊዜ «ጠላቂዎችን አልወድም» አለ።

فَلَمَّا رَأَى الْقَمَرَ بَازِغًا قَالَ هَٰذَا رَبِّي ۖ فَلَمَّا أَفَلَ قَالَ لَئِن لَّمْ يَهْدِنِي رَبِّي لَأَكُونَنَّ مِنَ الْقَوْمِ الضَّالِّينَ

ጨረቃንም ወጪ ኾኖ ባየ ጊዜ፦ «ይህ ጌታዬ ነው» አለ። በገባም ጊዜ፦ «ጌታዬ (ቅኑን መንገድ) ባይመራኝ በእርግጥ ከተሳሳቱት ሕዝቦች እኾናለሁ» አለ።

فَلَمَّا رَأَى الشَّمْسَ بَازِغَةً قَالَ هَٰذَا رَبِّي هَٰذَا أَكْبَرُ ۖ فَلَمَّا أَفَلَتْ قَالَ يَا قَوْمِ إِنِّي بَرِيءٌ مِّمَّا تُشْرِكُونَ

ፀሐይንም ጮራዋን ዘርግታ ባየ ጊዜ፦ «ይህ ጌታዬ ነው ። ይህ በጣም ትልቅ ነው» አለ ። በገባችም ጊዜ፦ «ወገኖቼ ሆይ! እኔ ከምታጋሩት ሁሉ ንጹሕ ነኝ» አለ።

إِنِّي وَجَّهْتُ وَجْهِيَ لِلَّذِي فَطَرَ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضَ حَنِيفًا ۖ وَمَا أَنَا مِنَ الْمُشْرِكِينَ

«እኔ ለዚያ ሰማያትንና ምድርን ለፈጠረው (አምላክ) ቀጥተኛ ስኾን ፊቴን አዞርኩ ። እኔም ከአጋሪዎቹ አይደለሁም» (አለ)።

- ✓ በዚህ መልኩ ካስተነተኑ በኋላ አላህ የማይታይ የማይዳሰስ አምሳያ የሌለው ብቸኛ አምላክ መሆኑን አሰቡ አላህም በጅብሪል አማካይነት ለአላህ ትእዛዝ እጅ እንዲሰጡ አዘዛቸው። እሳቸውም ለጌታቸው ትእዛዝ ፍፁም ታዛዥ መሆናቸውን አረጋገጡ።

ይህን እውነታ አላህ በተከበረው ቃሉ በላሚቷ ምእራፍ (ሱረቱል በቀራ) 131ኛው አንቀፅ ላይ እንዲህ ብሎ ይነግረናል:-

إِذْ قَالَ لَهُ رَبُّهُ أَسْلِمْ ۖ قَالَ أَسْلَمْتُ لِرَبِّ الْعَالَمِينَ

ጌታው ለርሱ ታዘዝ ባለው ጊዜ (መረጠው) ። ለዓለማት ጌታ ታዘዝኩ አለ

- ነብዩላሂ ኢብራሂም አላህ ለትእዛዙ እጅ እንዲሰጡ ካዘዛቸው በኋላ ፍፁም ታዛዥነታቸውን ገልፀው ዳዕዋ ጀመሩ። ማህበረሰባቸው አላህን አያውቅም። ቤተሰቦቻቸው ጣኦት ያመልካሉ ያለባቸው ሀላፊነት ክብደት እረፍት አልሰጣቸውም። ወደ አላህ መንገድ የመጣራቱን ሂደት ከጣኦት ቸርቻሪው አባታቸው መጀመር እንዳለባቸው ወሰኑ። ወደ አባታቸውም ሄደው አባቴ ሆይ አላህ ሰዎች እሱን ብቻ እንዲያመልኩ ልጣራ አዞኛል።

- **ዳዕዋዬን ካንተ መጀመር መረጥኩኝ እነዚህ የማይጠቅሙና የማይጎዱ የማይሰሙና የማያዩ ጣኦታትን ትተህ አላህን ብቻ ተገዛ እያሉ ወደ አላህ አምልኮት መጣራታቸውን አላህ በሱረቱል መርየም ከ41 – 45 ድረስ በሚከተለው መልኩ ይነግረናል:-**

وَاذْكُرْ فِي الْكِتَابِ إِبْرَاهِيمَ ۚ إِنَّهُ كَانَ صِدِّيقًا نَّبِيًّا

በመጽሐፉ ውስጥ ኢብራሂምንም አውሳ ። እርሱ በጣም እውነተኛ ነቢይ ነበርና።

إِذْ قَالَ لِأَبِيهِ يَا أَبَتِ لِمَ تَعْبُدُ مَا لَا يَسْمَعُ وَلَا يُبْصِرُ وَلَا يُغْنِي عَنكَ شَيْئًا

ለአባቱ ባለ ጊዜ (አስታውስ) «አባቴ ሆይ! የማይሰማንና የማያይን ከአንተም ምንንም የማይጠቅምህን (ጣዖት) ለምን ትግገዛለህ

يَا أَبَتِ إِنِّي قَدْ جَاءَنِي مِنَ الْعِلْمِ مَا لَمْ يَأْتِكَ فَاتَّبِعْنِي أَهْدِكَ صِرَاطًا سَوِيًّا

«አባቴ ሆይ! እኔ ከዕውቀት ያልመጣልህ ነገር በእርግጥ መጥቶልኛልና ተከተለኝ፡፡ ቀጥተኛውን መንገድ እመራሃለሁና፡፡

يَا أَبَتِ لَا تَعْبُدِ الشَّيْطَانَ ۖ إِنَّ الشَّيْطَانَ كَانَ لِلرَّحْمَٰنِ عَصِيًّا

«አባቴ ሆይ! ሰይጣንን አትግገዛ፡፡ ሰይጣን ለአልረሕማን አመጸኛ ነውና፡፡

يَا أَبَتِ إِنِّي أَخَافُ أَن يَمَسَّكَ عَذَابٌ مِّنَ الرَّحْمَٰنِ فَتَكُونَ لِلشَّيْطَانِ وَلِيًّا

«አባቴ ሆይ ! እኔ ከአልረሕማን ቅጣት ሊያገኝህ ለሰይጣንም ጓደኛ ልትኾን እፈራለሁ፡፡»

- ነብዩላሂ ኢብሪሂ በጣም ኸስዳናቂና ኸስተማሬ በሆነ መልኩ ክብር በተሞላበትና እኔ ኸዋቂ ነኝ የሚል የኩሪት ስሜት በሌለበት የሚገርም ኸካሄዳ ኸባቴ ሆዮ እያሉ ላዳሪጉት ለዚህ ጥሬ ከኸባታቸው የተቸሩት ምላሽ ተስፋ የሚያስቆርጥ ነበር ፡፡ የኸባታቸው ምላሽ ምን እንዳነበረ ኸላህ ሲነግረን እዛው በሱረቱል መርየም 46ኛው ኸንቀፅ እንዲህ ዶለናል:-

قَالَ أَرَاغِبٌ أَنتَ عَنْ آلِهَتِي يَا إِبْرَاهِيمُ ۖ لَئِن لَّمْ تَنتَهِ لَأَرْجُمَنَّكَ ۖ وَاهْجُرْنِي مَلِيًّا

(አባቱም) «ኢብራሂም ሆይ! አንተ አምላኮቼን ትተህ የምትዞር ነህን ባትከለከል በእርግጥ እወግርሃለሁ ፡፡ ረዥም ጊዜንም ተወኝ» አለ ፡፡

- **ይሁን እንጂ ነብዩላሂ ኢብራሂም በአባታቸው መልስ ተስፋ ቢቆርጡም ሳይበሳጩ የሰጡት መልስ በዛው ምእራፍ 47 ኛው አንቀፅ እንዲህ የሚል መሆኑ ተነግሮናል:-**

قَالَ سَلَامٌ عَلَيْكَ ۖ سَأَسْتَغْفِرُ لَكَ رَبِّي ۖ إِنَّهُ كَانَ بِي حَفِيًّا

«ደህና ኹን ፡፡ ወደፊት ከጌታዬ ምሕረትን እለምንልሃለሁ፡፡ እርሱ ለኔ በጣም ርኅሩኅ ነውና» አለ፡፡

➔ ነብየላሂ አብራሂም ዳዕዋቸው አባታቸው ዘንድ ፍሬ ባለማፍራቱ ስሜታቸው ቢጎዳም የዳዕዋ ገዘዋቸውን ከመቀጠል አላገዳቸውም ። በዘመኑ ወደ ነበረው ነምሩድ ወደ ሚባለው ንጉስ ሄደው ዳዕዋ ማድረግ ጀመረ የነመሞሩድ ባለሚሎች ጌታችን ነሞሩድ ነው የሚል መልስ ሲሰጡ ነብየላሂ አብራሂም በቆራጥነትና በአላህ ላይ በመመካት ነሞሩድ ጌታ እንዳልሆነና የሁላቸውም ፈጣሪ አላህ መሆኑን አስመልክቶ ያደረጉትን ዳዕዋ አላህ ሲነግረን እንዲህ ይለናል:-

قَالَ بَل رَّبُّكُمْ رَبُّ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ الَّذِي فَطَرَهُنَّ وَأَنَا عَلَىٰ ذَٰلِكُم مِّنَ الشَّاهِدِينَ

«አይደለም ጌታችሁ የሰማያትና የምድር ጌታ ያ የፈጠራቸው ነው ። እኔም በዚህ ላይ ከመስካሪዎቹ ነኝ» አለ።

➔የዚህን ጊዜ ነምሩድ ጌታ መሆኑን ሞገተ ። ነብዩላሂ ኢብሁሂምም አላህ ማለት ምን አይነት ጌታ እንደሆነና የነምሩድን ደካማነት ያስመሰከሩበትን መረጃ አላህ በሱረቱል በቀሁ 258 ኛው አንቀፅ ላይ ይነግረናል:-

أَلَمْ تَرَ إِلَى الَّذِي حَاجَّ إِبْرَاهِيمَ فِي رَبِّهِ أَنْ آتَاهُ اللَّهُ الْمُلْكَ إِذْ قَالَ إِبْرَاهِيمُ رَبِّيَ الَّذِي يُحْيِي وَيُمِيتُ قَالَ أَنَا أُحْيِي وَأُمِيتُ ۖ قَالَ إِبْرَاهِيمُ فَإِنَّ اللَّهَ يَأْتِي بِالشَّمْسِ مِنَ الْمَشْرِقِ فَأْتِ بِهَا مِنَ الْمَغْرِبِ فَبُهِتَ الَّذِي كَفَرَ ۗ وَاللَّهُ لَا يَهْدِي الْقَوْمَ الظَّالِمِينَ

ወደዚያ አላህ ንግሥናን ስለሰጠው ኢብራሂምን በጌታው ነገር ወደ ተከራከረው ሰው አላየህምን ኢብራሂም «ጌታዬ ያ ሕያው የሚያደርግና የሚገድል ነው» ባለ ጊዜ «እኔ ሕያው አደርጋለሁ እገድላለሁም» አለ። ኢብራሂም፡- «አላህ ፀሐይን ከምሥራቅ በኩል ያመጣል (አንተ) ከምዕራብ በኩል አምጣት» አለው። ያም የካደው ሰው ዋለለ፤ (መልስ አጣ) አላህም በዳዮች ሕዝቦችን አይመራም።

↳ነምሩድ በዚህ መልኩ ማላገጥ ሲጀምር አላህ አዋርዶት ነብዩላሂ ኢብራሚን በሐቅ ላይ የበላይ አድርጎ ተአምረኛው ጌታ ያ እኔ አምላክ ነኝ ሲል የነበረውን ነምሩድ አንድ ትንኝ በአፍንጫው ገብታ እራሱን እንኳን ከመከራ ማዳን እንደማይችል በማሳየት ለዘመናት ስታሰቃየው ቆይታ በዛው ፍጻሜው እንዲሆን አደረገው ።

↳ **ነብዩላሂ ኢብራሂም ዳዕዋቸውን ከንግግር ወደ ተግባር ለመቀየር ወሰኑ። ለጣኦት አምላኪያን የሚያመልኩዋቸው ጣኦታት ያልተገዛቸውን መጎዳትም ሆነ የተገዛቸውን መጥቀም እንደማይችሉ ከዚህም በላይ ራሳቸውንም ከጥቃት የማይከላከሉ መሆናቸውን ማሳየት እንዳለባቸው አመኑ።**

↳ የባአላቸው ቀን ጠብቀው ሁሉም ተሰባስበው ወደ በአሉ ሲሄዱ ነብዩላሂ ኢብራሂም መጥረጊያቸውን ተሸክመው ወደ ጣኦቶቻቸው አመሩ። የተለያየ ስለት እንዲሁም ምግብም አጠገባቸው ተቀምጦ አዩ!! አትበሉም እንዴ እያሉ ያናግሯቸው ጀመር መልስ የለም። ትልቁን ብቻ አስቀርተው ጣኦታቱን ፈላልጠው ጨረሱ። ከዛም መጠረቢያውን በትልቁ ጣኦት ላይ አስቀምጠው ጥለው ሄዱ። ጣኦትአምላኪያኖቹ ከባአል ማክበሪያ ሲመለሱ በጣኦቶቻቸው ላይ የተሰራውን ጉድ አዩ። ስለጣኦቶቻቸው ደካማነትና ስለራሳቸው ዐቅለቢስነት ከማሰብ ይልቅ በአማልክቶቻችን ላይ ማነው ይህን የሰራው እያሉ መጠያየቅ ጀመሩ። ኢብራሂም የሚባል ነው ተባለ ፈልገው ጠየቋቸው። እሷቸውም ትልቁን ጠይቁት የሚናገር ከሆነ ብለው መለሱ።

⇨ ይህን ክስተት ቁርኣን በሚቀጥለው የአል ንቢያ ምእራፍ ከ59 – 67 በዝርዝር ያስቀምጥልናል:-

قَالُوا مَن فَعَلَ هَٰذَا بِآلِهَتِنَا إِنَّهُ لَمِنَ الظَّالِمِينَ

«በአማልክቶቻችን ይህንን የሠራ ማነው እርሱ በእርግጥ ከበደለኞች ነው» አሉ።

قَالُوا سَمِعْنَا فَتًى يَذْكُرُهُمْ يُقَالُ لَهُ إِبْرَاهِيمُ

«ኢብራሂም የሚባል ጎበዝ (በመጥፎ) ሲያነሳቸው ሰምተናል» ተባባሉ።

قَالُوا فَأْتُوا بِهِ عَلَىٰ أَعْيُنِ النَّاسِ لَعَلَّهُمْ يَشْهَدُونَ

«ይመሰክሩበት ዘንድ በሰዎቹ ዓይን (ፊት) ላይ አምጡት» አሉ።

قَالُوا أَأَنتَ فَعَلْتَ هَٰذَا بِآلِهَتِنَا يَا إِبْرَاهِيمُ

«ኢብራሂም ሆይ! በአማልክቶቻችን ይህንን የሠራህ አንተ ነህን» አሉት።

قَالَ بَلْ فَعَلَهُ كَبِيرُهُمْ هَٰذَا فَاسْأَلُوهُمْ إِن كَانُوا يَنطِقُونَ

«አይደለም ይህ ታላቃቸው ሠራው። ይናገሩም እንደ ኾነ ጠይቋቸው» አለ።

فَرَجَعُوا إِلَىٰ أَنفُسِهِمْ فَقَالُوا إِنَّكُمْ أَنتُمُ الظَّالِمُونَ

ወደ ነፍሶቻቸውም ተመለሱ። «እናንተ (በመጠየቃችሁ) በዳዮቹ እናንተው ናችሁም» ተባባሉ።

ثُمَّ نُكِسُوا عَلَىٰ رُءُوسِهِمْ لَقَدْ عَلِمْتَ مَا هَٰؤُلَاءِ يَنطِقُونَ

ከዚያም በራሶቻቸው ላይ ተገለበጡ። «እነዚህ የሚናገሩ አለመኾናቸውን በእርግጥ ዐውቀሃል፤» (አሉ)።

➔የዘህን ገዜ ጥሩ መግቢያ አገኙ። ጠንከር ባለ ሁኔታ ዳዕዋ አደረጉላቸው። ይህንንም ቁርኣን በዛው ምእራፍ በሚቀጥለት አንቀፃች ላይ ይነግረናል:-

قَالَ أَفَتَعْبُدُونَ مِن دُونِ اللَّهِ مَا لَا يَنفَعُكُمْ شَيْئًا وَلَا يَضُرُّكُمْ

«ታዲያ ለእናንተ ምንም የማይጠቅማችሁንና የማይጎዳችሁን ነገር ከአላህ ሌላ ትገዛላችሁን» አላቸው።

أُفٍّ لَّكُمْ وَلِمَا تَعْبُدُونَ مِن دُونِ اللَّهِ ۖ أَفَلَا تَعْقِلُونَ

«ፎህ! ለእናንተ ከአላህ ሌላ ለምትገዙትም ነገር፤ አታውቁምን» (አለ)።

➔ጣኦት አምላኪያኑም በመሪጃ ሲሸነፉ ሐቅን ከመቀበል ይልቅ ወደ ሀይል ተሸጋገሩ ። ይህ የሁሉም የባጢል ተከታዮች ባህርይ ነው ። መሪጃ ሲያጡ ጡንቻን መሪጃ ያደርጋሉ ።

↳ **<u>ኢብራሂምንም አቃጥሉ ጣኦቶቻችሁንም እርዱ አሉ። ይህም እውነታ ቁርኣ በሚቀጥለው አንቀፅ ያስቀምጠዋል</u>**:-

قَالُوا حَرِّقُوهُ وَانصُرُوا آلِهَتَكُمْ إِن كُنتُمْ فَاعِلِينَ

«ሠሪዎች እንደ ኾናችሁ አቃጥሉት። አማልክቶቻችሁንም እርዱ» አሉ። (በእሳት ላይ ጣሉትም)።

- ✓ በቅሉ ቢሶቹም ነብዩላሂ ኢብራሂምን ሉጣቃጠል ወሰኑ። ጥፋታቸው ጣኦታትን ሌቁ ኣላህን ብቻ ተገዙ ማለታቸው ነው። በወቅቱ የነበረው መንግስት ግንብ ገንቡና እሳት ኣቀጣጥሉችሁ እዛ ውስጥ ጣሉት ብሎ ኣዘዘ።

ይህን ክስተት ቁርኣን እንዲህ ብሎ ይነግረናል:-

قَالُوا ابْنُوا لَهُ بُنْيَانًا فَأَلْقُوهُ فِي الْجَحِيمِ

«ለእርሱም ግንብን ገንቡ በእሳት ነበልባል ውስጥ ጣሉትም» አሉ።

↳ **በመንግስት ትእዛዝ ከፍታው 30 ሜትር ጎኑ የተራራ ጫፍ የሚሆን ምሽግ ተገነባ። ማንኛውም ህዝብ እንጨት እንዲሰበስብ ታዘዘ። ሴት ወንድ፣ አዋቂ ልጅ ሁሉም ወደ 40 ቀን አካባቢ ስራውን ትቶ መሰብሰብ ጀመረ። በዚህ ታይቶም ተሰምቶም በማይታወቅ ክምር እሳት ተለኮሰበት። ነበልባሉ ከሰማይ አሞራ ይጠልፍ ነበር ይባላል።**

↳ ጣኦት አምላኪያን ጉድ ተሰሩ። ኢብራሂምን እንዴት በዚህ እሳት ይወርውሩ? የሰው ሸይጣን መጥቶ ወስፈንጥር (ምንጀኒቅ) ዛሬ በዘመናዋ መልኩ መድፍ የሚባለው አይነት ማለት ነው እንዲሰሩና እዛ ላይ አድርገው እንዲወረውሩዋቸው ሐሳብ አቀረቡ። እንደተባሉት አደረጉ። በዚህ ሁኔታ ላይ እያሉ ጅብሪል መጣ ምን ትፈልጋለህ አላቸው? ነብየላሂ ኢብራሂምም ካንተ ምንም አልፈልግም። አላህ በቂዬ ነው ምን ያማረ መጠጊያ ነው አሉ ። ወዲያውም የአላህ እርዳታ መጣ። አላህ እሳትን አናገረ ። ይንንም ቁርኣን እንዲህ ብሎ አረጋገጠው :-

قُلْنَا يَا نَارُ كُونِي بَرْدًا وَسَلَامًا عَلَىٰ إِبْرَاهِيمَ(١)

«እሳት ሆይ! በኢብራሂም ላይ ቀዝቃዛ፤ ሰላምም ሁኚ» አልን።

(١) الأنبياء ٦٩

فَأَرَادُوا بِهِ كَيْدًا فَجَعَلْنَاهُمُ الْأَسْفَلِينَ(١)

በእርሱም ተንኮልን አሰቡ። ዝቅተኞችም አደረግናቸው።

- ነብዩላሂ ኢብራሂም ኣሳት ውስጥ ኣላህን ኣደወሱና ኣሱ ኣየሰገዱ ምንም ሳያሰጣቸው ቆዩ። ኣላህ መላኢካ ልኩ ደበስራቸው ነበር። ኣሳቱ ሲያቆም ነምሩድ የሆነውን ኢማየት ወጣ። ደየውን ማመን ኣቃተው ቆመው ኣየሰገዱ ነበር ደ ኢብራሂም ብዙ ተጣሉ ኣሳቸውም ከሶላታቸው ሲወጡ መልስ ሰጡት። ከዚህ ኣሳት ኣንዴት ዳንክ ኣላቸው የኔና ደንተ ጌታ ኣላህ ኣዳነኝ ኣሉት። ኣጌታህ ቁርጣን ኣቀርጣለሁ ኣላቸው ኣሳቸውም ኣላህ የከሀዲደንን ቁርጣን ኣያቀበልም ኣሉት።
- ከዚህ መዕጂዛ በኋላ የነምሩድ ህዘቦች ነብዩላሂ ኢብራሂምን የበለጠ ማሰቃየት ጀመሩ። ድግሞተኛ ነውም አሉ። በዚህን ጊዜ የአጎታቸው ልጅ ሳራና የወንድማቸው ልጅ ሉጥ ተከተሉዋቸው ዳዕዋቸውን ተቀበሉ። ሳራንም አገቡዋት።
- **አላህ ዒራቅን ትተው እንዲወጡ አዘዛቸው ሳራንና ሉጥን አስከትለው ከዒራቅ ምድር ወጡ። ዳዕዋ እያደረጉ ከዒራቅ ወደ ከንዓን (ፍልስጤን) ወደ ሻም ከዛም ወደ ግብፅ ምድር አመሩ። የግብፅ ምድር ሲደርሱ ዳንኳን ወጥረው አረፉ። ስለ ሳራ ቁንጅና ተሰራጨ።**

(١) الصاغات ٩٨

↳ንጉሱም ወታደሮቹን ልኮ ሳራን ከነብዩላህ ኢብራሂም ነጥሎ ወደ ቤተመንግስት አስወሰዳት ። ኢቀርባትም ከጀለ ዱዓእ ታደርግ ጀመር ። ሆዱ ላይ ህመም ተሰማው ተዋት ። ጌታሽን ለምኝልኝ አልነካሽም አላት ። ዱዓእ አደረገችለት ተሻለው ። መልሶ ከጀላት ። አሁንም ዱዓእ አደረገቸበት ህመም ተሰማው‼ ጌታሽን ለምኝልኝ አልነካሽም አላት ። ዱዓእ አደረገችለት ። አሁንም ከጀላት ዱዓኡ ቀጠለ ተመልሶ ታመመ ከዚህ በኋላ አላስብም ዱዓእ አድርጊልኝ አላት አደረገችለት ተሻለው።

↳ መታደሮቹን ጠርቶ ላጃርን በለጦታ ሰጥቶ ኬላም ጨምሮ ሂዱ ወዳመጣቹበት መልሷት ኻለ ። ወዳ ኢብራሂም ተመለሰች ።

↳ አላህ ሉጥን ነብይ አድርጎ ወደ ሶደም ህዝቦች ላከው። ነብዩላሂ ኢብራሂም ሳራን ይዘው ወደ ሻም ተመለሱ። ነብዩላሂ ኢብራሂም ዘር እንዲሰጣቸው አላህን ለመኑ። ሳራ መሀን ነበረች። ልጅ ወልዳ የባልዋን የልጅ ፍላጎት ባለሟሟላቷ ተሰማት። የዚህን ጊዜ ነብዩላሂ ኢብራሂም ቁጭ ብለው አላህ እንዴት ነው ሙታንን ህያው የሚያደርገው ብለው ያስተነትኑ ነበር። አላህንም ሙታንን እንዴት ህያው እንደምታደርግ አሳየኝ አሉ። ወዲያ ጂብሪል መጥቶ አላመንክም እንዴ ብሎ ጠየቃቸው። እሳቸውም አምኛለሁ ግን ልቤ ሲረጋጋልኝ ነው አሉ።

➢ **ይህን ሁኔታ አላህ በላሚቷ ምእራፍ 260 ኛው አንቀፅ ላይ እንዲህ ብሎ ይነግረናል**:-

وَإِذْ قَالَ إِبْرَاهِيمُ رَبِّ أَرِنِي كَيْفَ تُحْيِي الْمَوْتَىٰ ۖ قَالَ أَوَلَمْ تُؤْمِن ۖ قَالَ بَلَىٰ وَلَٰكِن لِّيَطْمَئِنَّ قَلْبِي ۖ قَالَ فَخُذْ أَرْبَعَةً مِّنَ الطَّيْرِ فَصُرْهُنَّ إِلَيْكَ ثُمَّ اجْعَلْ عَلَىٰ كُلِّ جَبَلٍ مِّنْهُنَّ جُزْءًا ثُمَّ ادْعُهُنَّ يَأْتِينَكَ سَعْيًا ۚ وَاعْلَمْ أَنَّ اللَّهَ عَزِيزٌ حَكِيم

ኢብራሂምም «ጌታዬ ሆይ! ሙታንን እንዴት ሕያው እንደምታደርግ አሳየኝ» ባለ ጊዜ (አስታውስ፡፡) አላህ ፡- «አላመንክምን» አለው፡፡ «አይደለም (አምኛለሁ)፤ ግን ልቤ እንዲረጋ» ነው አለ፡፡ (አላህም)፡- «ከበራሪዎች (ከወፎች) አራትን ያዝ፡፡ ወደ አንተም ሰብስባቸው፡፡ (ቆራርጣቸውም)፤ ከዚያም በየኮረብታው ሁሉ ላይ ከነርሱ ቁራጭን አድርግ፡፡ ከዚያም ጥራቸው፤ ፈጥነው ይመጡሃልና፡፡ አላህም አሸናፊ ጥበበኛ መኾኑን ዕወቅ» አለው፡፡

⇨ ሳሬ ለነብዩላሂ ኢብራሂም ኣላህ ዘር ኣንዲሰጣቸው ሀጆርን ኣንዲደገቡዋት ኣጸሊገች። ተጋቡም። ሃጆርም·ፀነሰች። ሀጆር ኣርግዝናዋን ለመጸበቅ መቀነት ታስር ነበር። መቀነት የጆመሊችውም ኣሷ ነች ይባላል። ሳሬ መፀነስዋን ባወቀች ጊዜ የቅናት ስሜት ተሰማት ኣኔና ኣሷ ኣንጽ ሀገር ላይ መኖር ኣንችልም ፊቷን ዞር ኣጽርግልኝ ኣለቻቸው። ሀጆርም ነብዩላሂ ኢስማኢልን ወለጸች።

⇨ አላህ ለነብዩላሂ ኢብራሂም ሀጀርና ህፃኑን ይዘው ከሻም እንዲወጡ አዘዛቸው፡፡ በጅብሪል ጓደኝነት ጉዞ ጀመሩ መካ በደረሱ ጊዜ ጅብሪል አሁን በሶፋ ኮረብታና በዘምዘም ጉድጓድ መሀል ላይ ባለው ቦታ እዚህ እረፉ አላቸው፡፡ ነብዩላሂ ኢብራሂም የያዙትን ተምርና ውሃ አስቀምጠውላቸው መሄድ ጀመሩ፡፡

⇨ **ሀጀር ስታይ በቦታው እንኳን ሰው እንሰሳም ይሁን አእዋፍት የለም። ድንጋይና አሸዋ ብቻ ነው ያለው። እልም ያለ በረሀ ነው ሙቀቱ ከሚገመተው በላይ ነው።**

⇨ ሃጀር ያ ኢብራሂም እያለች ተጣራች ዘሞ አሉ ደጋግማ ተጣራች ዘሞ አሉ ወደፈት እየሄዱ ነው። ድምፃን ከፍ አድርጋ አላህ ነው እንዴ ያዘዘህ አለቻቸው አው አሏት። እንግዲያውስ አላህ አይጥለንም አለቻቸው።

⇨ **ነብዩላሂ ኢብራሂም የአላህን ትእዛዝ ለሞምላት ውስጣቸው እየተረበሸ ከእይታዋ ተሰወሩ ። ከዛም የሚከተለውን ዱዓእ አደረጉ:-**

رَّبَّنَا إِنِّي أَسْكَنتُ مِن ذُرِّيَّتِي بِوَادٍ غَيْرِ ذِي زَرْعٍ عِندَ بَيْتِكَ الْمُحَرَّمِ رَبَّنَا لِيُقِيمُوا الصَّلَاةَ فَاجْعَلْ أَفْئِدَةً مِّنَ النَّاسِ تَهْوِي إِلَيْهِمْ وَارْزُقْهُم مِّنَ الثَّمَرَاتِ لَعَلَّهُمْ يَشْكُرُونَ(١)

"ጌታችን ሆይ! እኔ አዝመራ በሌለው ሸለቆ ውስጥ በተከበረው ቤት (በካዕባ) አጠገብ ከዘሮቼ አስቀመጥኩ። ጌታችን ሆይ! ሶላትን ያቋቁሙ ዘንድ (አስቀመጥኳቸው)። ከሰዎችም ልቦችን ወደእነሱ የሚናፍቁ አድርግ። ያመሰግኑህም ዘንድ ከፍሬዎች ስጣቸው።"

➔ **ሃጀር ተምሩን እየበላች ከውሀው እየጠጣች ልጇን ማጥባት ጀመረች። ነገር ግን ተምሩም ውሀውም አለቀ ። ህፃኑ በረሀብ ማልቀስ ጀመረ።**

(١) إبراهم ٣٧

➔ ሃጀር የህፃኗ ረሀብና ለቅሶ ረፍት ነሳት ረሀቡ በህፃኑ ላይ እየበረታ ሄደ ለቅሶዉም እየጨመረ ሄደ። እናት የልጇን ስቃይ ማየት አቃታት ተነስታ ቆማ ታማትር ጀመር። የሶፋ ኮረብታ ቅርብ ሆኖ አየችው ወደዛ ሄደች ኮረብታው ላይ ወጥታ ግራና ቀኝ ማማተር ጀመረች። ምናልባት ከሩቅ የሚታይ ነገር ቢኖር ብላ ምንም የለም ። ከሶፋ 30 መቶ ሜትር አካባቢ ርቆ የመርዋ ኮረብታ ታያት። ወርዳ ወደዛ አመራች የተወሰነ ቦታ በሶምሶማ ሄደች መቀጠል ግን አልቻለችም ቀስ ብላ ደረሰች። ወደ ኮረብታው ወጥታ ማማተር ጀመረች። ምንም ነገር የለም ጭንቀቷ ጨመረ ወደ ህፃኑ ዞር ብላ ስታይ ጨኸቱ በድካም ቀንሶ በጣረ ሞት በእግሩ መሬት እየመታ አየችው። ምድሩ ጠበባት እየሆነ ያለው ነገር እውነት አልመስልሽ አላት። ወደ ሶፋ ሄዳ እንደመጀመሪያ አደረገች። ወረደች ወደ መርዋ ሄደች እዛም እንደተለመደው አደረገች። በዚህ መልኩ በሶፋና በመርዋ 7 ጊዜ ተዘዋወረች።

➔ መርዋ ላይ ሆኗ ስታማትር የሆነ ድምፅ ሰማች ለራሷ እስኪ ዝም በይ አለች። አሁንም ድምፅ ሰማች ሲሞት ላለማየት ወደ ህፃኗ ማየት አትፈልግም ነበረ። ድምፁ በልጇ አቅጣጫ ነበር ማሰማቱስ አሰማህ የምትረዳው ነገር ካለህ አለች። ዞር ስትል ጅብሪል በክንፉ ከልጇ እግር ስር ሲመታ አየች ወዲያ ምንጭ ፈለቀ። የሞት ሞቷ ደረሰች ምንጩን ሁለት እጆቿን ዘርግታ ዘም ዘም (እትሂድ አትሂድ) እያለች ትከበው ጀመር ስሙም ዘምዘም ተባለ። ጠጣች ልጇንም አጠባች። እሷም ልጇም በሚገርም ሁኔታ ሀይል አገኙ።

↳ ኣላህ በዚህ መልኩ የሀጃርን ኣላህ ከሆነ ጀዘዘህ ኣይጥላንም ጀላችበትን ተወኩል ኣውን ኣጸፊገው።

↳ ከየመን ወደ ሻም የሚሄዱ ነጋዴዎች አሞሁ ሲያንዣብብ ተመለከቱ ። እስከዛሬ ድረስ በዚህ ስናልፍ አሞሁ ሲያንዣብብ አይተን አናውቅም አንድ የተከሰተ ነገር ቢኖር ነው አሞሁ የሚያንዣብበው ውሀ ባለበት አካባቢ ነውና እስኪ ሄዳችሁ እዩ ተብሎ ሁለት ሰዎች ተላኩ ። ሰዎቹም ሃጀርና ህፃኗ ውሀ አጠገብ ሆነው አዩ ተመልሰው ያዩትን ተናገሩ ። ሃጀርን ከሷ ጋር ለመኖር ትፈቅድላቸው እንደሆነ ጠየቋት እሷም ከውሀው መብት የላችሁም እኔ ነኝ ባለቤቱ መቀመጥ ትችላላችሁ አለቻቸው ።

↳ ጁርሁም የሚባሉት የየመን ሰዎች ቤተሰቦቻቸውን ይዘው መጥተው ከሃጀር ጋር መኖር ጀመሩ። እነርሱ የምትፈልገውን ነገር እያቀረቡ እሷ ከዘምዘም ውሀ ትሰጣቸዋለች። በዚህ መልኩ መካ ተቆረቆረች።

↳ ነብዩላሂ ኢብራሂም ዘንድ 3 እንግዶች መጡ መልካቸው በጣም አስገራሚ ነበር ። ነብዩላሂ ኢብራሂም ከኔ በስተቀር ማንም አያስተናግዳቸውም አሉ። ራሳቸው ምግብ ሰሩላቸው አቀረቡ ነገር ግን አይበሉም። ይህን ታሪክ አላህ በዛሪያት ምእራፍ ከ24 – 28 አንቀፅ እንዲ ብሎ ይነግረናል:-

هَلْ أَتَاكَ حَدِيثُ ضَيْفِ إِبْرَاهِيمَ الْمُكْرَمِينَ

የተከበሩት የኢብራሂም እንግዶች ወሬ መጥቶሃልን?

إِذْ دَخَلُوا عَلَيْهِ فَقَالُوا سَلَامًا ۖ قَالَ سَلَامٌ قَوْمٌ مُّنكَرُونَ

በእርሱ ላይ በገቡና «ሰለም» ባሉ ጊዜ (አስታውስ) ። «ሰላም ያልታወቃችሁ ሕዝቦች ናችሁ፤» አላቸው ።

فَرَاغَ إِلَىٰ أَهْلِهِ فَجَاءَ بِعِجْلٍ سَمِينٍ

ወደ ቤተሰቡም ተዘነበለ፤» ወዲያውም የሰባ ወይፈንን አመጣ።

فَقَرَّبَهُ إِلَيْهِمْ قَالَ أَلَا تَأْكُلُونَ

ወደእነርሱም (አርዶና ጠብሶ) አቀረበው። «አትበሉም ወይ?» አላቸው።

فَأَوْجَسَ مِنْهُمْ خِيفَةً ۖ قَالُوا لَا تَخَفْ ۖ وَبَشَّرُوهُ بِغُلَامٍ عَلِيمٍ

ከእነርሱ መፍራትንም በልቡ አሳደረ። «አትፍራ» አሉት ። በዐዋቂ ወጣት ልጅም አበሰሩት።

- ነብየላሂ ኢብራሂም ቤተሰባቸውን እማየት ከሻም ወደ መካ መጡ። ልጃቸውን ኢስማኢልን ሲያዩ ከሚጠብቁት በላይ ተደሰቱ። ኢስማኢል ወደ 14 አመታቸው አካባቢ ሆኗል። እአላህ የሰጡት አደራ በሚገርም ሁኔታ ተጠብቋል። የልጃቸው እድገትና ሁኔታ ትልቅ ደስታ ፈጥሮባቸዋል። ፍቅሩ በውስጣቸው ገባ አላህ ነብየላሂ ኢብራሂም ከአላህ ውጪ የሌላ ነገር ፍቅር ውስጣቸው እንዲገባ አይፈቅድም። ነብየላሂ ኢብራሂም በመናማቸው ኢስማኢልን ሲያርዱት አየ የነብያት መናም እውነት ነውና ለኢስማኢል ነገሩት ኢስማኢልም አባቴ ሆይ የታዘዘከውን ፈፅም ከታጋሾች ሆኜ ታገኝኛለህ አላቸው።

- ነብዩሳሂ ኢብራሂምም ኢስማኢልን ይዘው ወደ ማረጃው ቦታ ማምራት ጀመሩ። መንገድ ሳይ ሸይጣን ኢስማኢልን ከባትህ መናም ማየቱን ኸንዴት ከመንክ ኸያስ ይወሰውስ ጀመር። ኢስማኢልም ጠጠር ከንስተው በሸይጣን ሳይ ይወረውሩ ጀመር። ኸናቱ ጋር ሄዶ መወትወት ጀመረ። ተመሳሳይ ነገር ገጠመው።

- ቦታው ላይ ሲደርሱ ነብዩላሂ ኢብራሂም ኢስማኢልን ሊያርዱዋቸው አስተኙዋቸው። የነብዩላሂ ኢብራሂም ሁኔታ ያየው ኢስማኢል በፊት ለፊቴ አስተኛኝና በማጅራቴ በኩል እረደኝ አላቸው ይላሉ አንዳንድ ዘገባዎች። አስተኝተው ሊያርዱት ሲሉ ጅብሪል ሙክት ይዞ መጥቶ በኢብራሂም ፈንታ ይህን እረድ አላቸው።

- ኰላህ የኒሳገው የኢስማኢል መታረጃ ሳይሆን ኰባትና ልጅ አኰላህ ትኰዛዝ ያላቸውን ቦታ ማሳየት ነበርና ታይቷል ።

☞ ***<u>ይህን ክስተት ቁርኣን በሷፋት ምእራፍ ከ102 – 107 ድረስ ይነግረናል:-</u>***

فَلَمَّا بَلَغَ مَعَهُ السَّعْيَ قَالَ يَا بُنَيَّ إِنِّي أَرَىٰ فِي الْمَنَامِ أَنِّي أَذْبَحُكَ فَانظُرْ مَاذَا تَرَىٰ ۚ قَالَ يَا أَبَتِ افْعَلْ مَا تُؤْمَرُ ۖ سَتَجِدُنِي إِن شَاءَ اللَّهُ مِنَ الصَّابِرِينَ

ከእርሱ ጋርም ለሥራ በደረሰ ጊዜ «ልጄ ሆይ! እኔ በሕልሜ እኔ የማርድህ ሆኜ አያለሁ። ተመልከትም፤ ምን ታያለህ?» አለው። «አባቴ ሆይ! የታዘዝከውን ሥራ። አላህ ቢሻ ከታጋሾቹ ሆኜ ታገኘኛለህ» አለ።

فَلَمَّا أَسْلَمَا وَتَلَّهُ لِلْجَبِينِ

ሁለቱም ትዕዛዙን በተቀበሉና በግንባሩም ጎን ላይ በጣለው ጊዜ (የሆነው ሆነ)።

وَنَادَيْنَاهُ أَن يَا إِبْرَاهِيمُ

ጠራነውም፤ (አልነው) «ኢብራሂም ሆይ!

قَدْ صَدَّقْتَ الرُّؤْيَا ۚ إِنَّا كَذَٰلِكَ نَجْزِي الْمُحْسِنِينَ

ራእይቱን በእውነት አረጋገጥክ።» እኛ እንደዚሁ መልካም ሠሪዎችን እንመነዳለን።

إِنَّ هَٰذَا لَهُوَ الْبَلَاءُ الْمُبِينُ

ይህ እርሱ በእውነት ግልጽ ፈተና ነው።

وَفَدَيْنَاهُ بِذِبْحٍ عَظِيمٍ

በታላቅ ዕርድም (መስዋዕት) ተቤዠነው።

- ✓ የነብዩላሂ ኢብራሂም የሃጀርና ኢስማኢል ታሪክ በአብዛኛው ከሀጅ ስራ ጋር ይገናኛል። በየአመቱ ዒደል አድሓ ቀን የሚታረደው እርድም ይህን ታላቅ ክስተት ለማስታወስ ነው።

✓ ነብዩላሂ ኢብራሂም የጌታቸውን ትእዛዘ ብቸኛ ልጃቸውን በማረድ ለመፈፀም ባሳዩት ቁርጠኛና አስገራሚ አቋም አላህ ሌላ ልጅም እንደሚሰጣቸው ብስራት ላከላቸው። ይህም በተከበረው ቃሉ ከመጀመሪያ ሚስታቸው ሳራ ኢስሓቅና የልጅ ልጃቸው የዕቆብም የሚሰጣቸው መሆኑን በሚቀጥለው የሁድ ሞእራፍ 71ኛው ላይ አንቀፅ እንዲህ ብሎ ይነግረናል:-

وَامْرَأَتُهُ قَائِمَةٌ فَضَحِكَتْ فَبَشَّرْنَاهَا بِإِسْحَاقَ وَمِن وَرَاءِ إِسْحَاقَ يَعْقُوبَ

ሚስቱም የቆመች ስትኾን (አትፍራ አሉት) ሳቀችም። በኢስሐቅም አበሰርናት። ከኢስሐቅም በኋላ (በልጁ) በያዕቁብ (አበሰርናት)።

✓ **ሳራ እኔ አሮጊት ሆኜ ባለቤቴም ሸማግሌ ሆኖ ሳለ እወልዳለሁኝ እንዴ አለች በመገረም። መላኢካዎችም በአላህ ጉዳይ ትገረሚያለሽን አሉ። አላህ ሁሉን ቻይ ነውና ያሻውን ይሰራል። እሱ ካሻ ከአሮጊት ማህፀን ነብይ ይፈጥራል። ይህንንም በዛው ምእራፍ ቀጥሎ ባለው አንቀፅ ይነግረናል:-**

قَالَتْ يَا وَيْلَتَىٰ أَأَلِدُ وَأَنَا عَجُوزٌ وَهَٰذَا بَعْلِي شَيْخًا ۖ إِنَّ هَٰذَا لَشَيْءٌ عَجِيبٌ

(እርሷም) ዋልኝ! እኔ አሮጊት ይህም ባሌ ሸማግሌ ሆኖ ሳለ እወልዳለሁን ይህ በእርግጥ አስደናቂ ነገር ነው አለች ።

قَالُوا أَتَعْجَبِينَ مِنْ أَمْرِ اللَّهِ ۖ رَحْمَتُ اللَّهِ وَبَرَكَاتُهُ عَلَيْكُمْ أَهْلَ الْبَيْتِ ۚ إِنَّهُ حَمِيدٌ مَّجِيدٌ

«ከአላህ ትዕዛዝ ትደነቂያለሽን የአላህ ችሮታና በረከቶቹ በእናንተ በኢብራሂም ቤተሰቦች ላይ ይሁን እርሱ ምስጉን ለጋስ ነውና» አሉ ።

- ✓ ነብዩላሂ ኢብራሂም ኢስማኢልን ለማረድ ወስነው አላህ በሙክት ቀይሮላቸው ካበሰራቸው በኋላ ወደ ሻም ተመልሰው ወደ አላህ አምልኮ ይጣሩ ጀመር።
- ✓ ኢስማኢልም አደጉ እድሜያቸውም ለነብይነት ደረሰ አላህ ነብይ አደረጋቸው። ዳዕዋ ማድረግ ጀመሩ ከጁርሁም ጎሳዎችም የሆነች ሴት አገቡ።

⇨ ነብዩላሂ ኢብራሂም ቤተሰባቸውን ለማየት ወደ መካ መጡ። ነብዩላሂ ኢስማኢል ለአደን ወጥተዋል። ሚስትየውን አገኙ ስለኑሯቸው ጠየቋዋት በጣም በችግር ነው ያለነው። አዝመራም የለም። ምግብም ውሀም የለም ረሀብና ጥም ነው አለቻቸው። አላህ በወሰነው ነገር ባለመውደድዋ ደስ አላላቸውም። ባለቤትሽ ሲመጣ የቤትህን መቃን ቀይረው ብለኋል ብለሽ ንገሪው ብለው ወደ ሻም ተመለሱ።

⇨ ነብዩላሂ ኢስማኢል ከአደን ተመለሱ። የመጣ ሰው ነበር ወይ ብለው ጠየቁ አው አንድ ሽማግሌ እንግዳ መጥቶ ነበር አለችው። ምን ጠየቀሽ አሉ ስለነሪችን ጠየቀኝ ከዛም ያለንበትን ችግር ነገርኩት አለች። ያለሽ ነገር አለን አሉዋት አው የቤትህን መቃን ቀይር በይው ብሎኛል አለች። እሱ አባቴ ነው የቤቴ መቃን አንቺ ነሽ ፍታት ብሎኛል ወደ ቤተሰቦችሽ ሂጂ አሏት (ፈቱዋት)።

⇨ ነብዩላሂ ኢስማኢል ሌላ የአንድ ምስኪን ልጅ አገቡ በጣም አላህን የምትፈሩ ባለው የምትብቃቃ ለባልዋ ታዛዥ ነበረች ። ነብዩላሂ ኢስማኢል በደስታ ወደ አላህ መገዛት እየተጣሩ መኖር ጀመሩ ። አንድ ቀን እንደ ልማዳቸው ወደ አደን ሄዱ ።

- ነብዮካሂ ኢብሌሂም ቤተሰባቸውን ሐማየት መጡ። ልጃቸው የሐም። ሁለተኛዋን ሚስት አገኙዋት ። አንግዳ ትወዳላችሁ ወይ? ለአንግዳስ የምታቀርቡት ነገር አለ ወይ ብለው ሰላምታ አቅርበው ገቡ። ሚስትየውም አልሐምዱ ሊላህ ምን ጠፍቶ ሁሉ ነገር አለ ግቡ አለች። ነብዮካሂ ኢብሌሂምም በሁኔታዋና መልኳ በጣም ተደሰቱ ። ምግችሁ ምንድነው አሏት ስጋ አለቻቸው። መጠጣችሁስ ምንድነው አሏት ውሀ (የዘምዘም ውሀ) አለች ። ጹዳኔ አጸፊጉላቸው። ባለቤትሽ ሲመጣ የቤትህን መቃን አጥብቀው ጥሉ መቃን ነው በይው ብሎኛል አለችው። እሳቸውም እሱ አባቴ ነው መቃኗ አንቺ ነሽ በደንብ ያዛት ማለቱ ነው አሉዋት።

- ነብየላሂ አስማኢል ከአደን ሲመለሱ የመጣ ሰው ነበር ወይ ብለው ጠየቅዋት። አው ብላ የሆነውን ነገረቻቸው። ሞን አለሽ አሉዋት ባለቤትሽ ሲመጣ የቤትህን መቃን አጥብቀው ጥሩ መቃን ነው በይው ብሎኛል አለችው። እሳቸውም እሱ አባቴ ነው መቃኗ አንቺ ነሽ በደንብ ያዛት ማለቱ ነው አሉዋት።

- **ነብየላሂ ኢብራሂም ለሶስተኛ ጊዜ ቤተሰባቸውን ለማየት ወደ መካ መጡ። ነብየላሂ አስማኢል ቀስት እየሰሩ አገኟቸው። ሁለቱም ተያዩ አባት በልጁ ላይ ልጅም በአባቱ ላይ እንደሚያደርገው ተቃቅፈው ተሳሳሙ። ነብየላሂ ኢብራሂም ካዕባን ከልጃቸው አስማኢል ጋር ሆነው መሰረቱን ከፍ አድርገው እንዲገነቡ አላህ ያዘዛቸው መሆኑን ነገራቸው። ነብየላሂ አስማኢልም በጣም ተደሰቱ። ካዕባንም መገንባት ጀመሩ።**

⇒ ***<u>ይህን ክስተትና ከግንባታው ጋር የተገናኙ ሁለቱም ያደረጓቸው ዱዓኦችን አላህ በላሚቷ ምእራፍ ከ25 – 30ኛው አንቀፅ ላይ እንዲህ ብሎ ይነግረናል</u>*** :-

وَإِذْ جَعَلْنَا الْبَيْتَ مَثَابَةً لِّلنَّاسِ وَأَمْنًا وَاتَّخِذُوا مِن مَّقَامِ إِبْرَاهِيمَ مُصَلًّى ۖ وَعَهِدْنَا إِلَىٰ إِبْرَاهِيمَ وَإِسْمَاعِيلَ أَن طَهِّرَا بَيْتِيَ لِلطَّائِفِينَ وَالْعَاكِفِينَ وَالرُّكَّعِ السُّجُودِ

ቤቱንም ለሰዎች መመለሻና ጸጥተኛ ባደረግን ጊዜ (አስታውስ) ። ከኢብራሂምም መቆሚያ መስገጃን አድርጉ ። ወደ ኢብራሂምና ወደ ኢስማዒልም ቤቴን ለዘዋሪዎቹና ለተቀማጮቹም ለአጎንባሾች ሰጋጆቹም አጥሩ ስንል ቃል ኪዳን ያዝን።

وَإِذْ قَالَ إِبْرَاهِيمُ رَبِّ اجْعَلْ هَٰذَا بَلَدًا آمِنًا وَارْزُقْ أَهْلَهُ مِنَ الثَّمَرَاتِ مَنْ آمَنَ مِنْهُم بِاللَّهِ وَالْيَوْمِ الْآخِرِ ۖ قَالَ وَمَن كَفَرَ فَأُمَتِّعُهُ قَلِيلًا ثُمَّ أَضْطَرُّهُ إِلَىٰ عَذَابِ النَّارِ ۖ وَبِئْسَ الْمَصِيرُ

ኢብራሂም ባለ ጊዜ (አስታውስ)። ጌታዬ ሆይ! ይህንን ጸጥተኛ አገር አድርግ። ቤተሰቦቹንም ከነሱ በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነውን ሰው ከፍሬዎች ስጠው ። (አላህም) የካደውንም ሰው፤ (እሰጠዋለሁ)። ጥቂትም እጠቅመዋለሁ፤ ከዚያም ወደ እሳት ቅጣት አስጠጋዋለሁ፤ ምን ትከፋም መመለሻ! (አለ)።

وَإِذْ يَرْفَعُ إِبْرَاهِيمُ الْقَوَاعِدَ مِنَ الْبَيْتِ وَإِسْمَاعِيلُ رَبَّنَا تَقَبَّلْ مِنَّا ۖ إِنَّكَ أَنتَ السَّمِيعُ الْعَلِيمُ

ኢብራሂምና ኢስማኢልም «ጌታችን ሆይ! ከእኛ ተቀበል። አንተ ሰሚውና ዐዋቂው አንተ ነህና» የሚሉ ሲኾኑ ከቤቱ መሠረቶቹን ከፍ ባደረጉ ጊዜ (አስታውስ)።

رَبَّنَا وَاجْعَلْنَا مُسْلِمَيْنِ لَكَ وَمِن ذُرِّيَّتِنَا أُمَّةً مُّسْلِمَةً لَّكَ وَأَرِنَا مَنَاسِكَنَا وَتُبْ عَلَيْنَا ۖ إِنَّكَ أَنتَ التَّوَّابُ الرَّحِيمُ

«ጌታችን ሆይ! ላንተ ታዛዦችም አድርገን። ከዘሮቻችንም ላንተ ታዛዥች ሕዝቦችን (አድርግ)። ሕግጋታችንንም አሳየን፤ (አሳውቀን)። በኛም ላይ ተመለስን፤ አንተ ጸጸትን ተቀባዩ ሩኅሩኅ አንተ ብቻ ነህና።»

رَبَّنَا وَابْعَثْ فِيهِمْ رَسُولًا مِّنْهُمْ يَتْلُو عَلَيْهِمْ آيَاتِكَ وَيُعَلِّمُهُمُ الْكِتَابَ وَالْحِكْمَةَ وَيُزَكِّيهِمْ ۚ إِنَّكَ أَنتَ الْعَزِيزُ الْحَكِيمُ

«ጌታችን ሆይ! በውስጣቸውም ከነሱው የኾነን መልክተኛ በነርሱ ላይ አንቀጾችህን የሚያነብላቸውን መጽሐፍንና ጥበብንም የሚያስተምራቸውን (ከክህደት) የሚያጠራቸውንም ላክ፤ አንተ አሸናፊው ጥበበኛው አንተ ብቻ ነህና» (የሚሉም ሲኾኑ)።

وَمَن يَرْغَبُ عَن مِّلَّةِ إِبْرَاهِيمَ إِلَّا مَن سَفِهَ نَفْسَهُ ۚ وَلَقَدِ اصْطَفَيْنَاهُ فِي الدُّنْيَا ۖ وَإِنَّهُ فِي الْآخِرَةِ لَمِنَ الصَّالِحِينَ

ከኢብራሂምም ሕግጋት ነፍሱን ያቄለ ሰው ካልኾነ በስተቀር የሚያፈገፍግ ማነው? (የለም)፤ በቅርቢቱም ዓለም በእርግጥ መረጥነው። በመጨረሻይቱም ዓለም እርሱ ከመልካሞቹ ነው።

- አላህ ለነብየላሂ ኢብራሂም የካዕባን ቦታ አመላክቷቸው ከገቡ በኋላ ካዕባን ገንብተው ጨረሱ። አላህም ለሐጅ ጥሪ እንዲያደርጉ አዘዛቸው። እሳቸውም ጌታዬ ሆይ እንዴት አሰማለሁ አሉ። አላህ አንተ ተጣራ እኔ አሰማለሁ አላቸው። ተጣሩም። አላህ ጥሪው እንዲሰሙ ካደረጋቸው ነፍሶች ውስጥ በዛን ጊዜ የነበሩና የቻሉ እንዲመጡ አደረጋቸው። ነብየላሂ ኢብራሂምም የመጡትን የሐጅን ስርኣት አስተማሯቸው። እነዚያ ስርኣቶች ናቸው ሐጅ ላይ የሚከናወኑት ። ይህ ክስተት በሐጅ ምእራፍ ላይ በሰፊው ተብራርቷል። ከዛውስጥ 26ኛውና 27ኛውን አንቀፅ ቀጥሎ እንመልከት:–

وَإِذْ بَوَّأْنَا لِإِبْرَاهِيمَ مَكَانَ الْبَيْتِ أَن لَّا تُشْرِكْ بِي شَيْئًا وَطَهِّرْ بَيْتِيَ لِلطَّائِفِينَ وَالْقَائِمِينَ وَالرُّكَّعِ السُّجُودِ

ለኢብራሂምም የቤቱን (የካዕባን) ስፍራ መመለሻ ባደረግንለት ጊዜ «በእኔ ምንንም አታጋራ፣ ቤቴንም ለሚዞሩትና ለሚቆሙበት ለሚያጎነብሱትና በግንባራቸውም ለሚደፉት ንጹሕ አድርግላቸው» (ባልነው ጊዜ አስታውስ)።

وَأَذِّن فِي النَّاسِ بِالْحَجِّ يَأْتُوكَ رِجَالًا وَعَلَىٰ كُلِّ ضَامِرٍ يَأْتِينَ مِن كُلِّ فَجٍّ عَمِيقٍ

(አልነውም) ፡- በሰዎችም ውስጥ በሐጅ ትዕዛዝ ጥራ። እግረኞች ከየሩቅ መንገድ በሚመጡ ከሲታ ግመሎችም ሁሉ ላይ ሆነው ይመጡሃልና።

- ከዚህ በኋላ ነብዩላሂ ኢብራሂም መካ ላይ ተረጋግተው መኖር ጀመሩ። የኢስሐቅን ልጅ ነብዩላሂ የዕቆብን ካዩ በኋላ ወደ አኼራ ሄዱ።

የነብዮካሂ ኢብራሂም አጭር የህይወት ታሪክ በዚህ ተፈፀመ ።

በኡስታዝ አቡ ዑበይዳህ ባህሩ ተካ በተከታታይ በቴሌግራም ቻናል ቀርቦ **በወንድም አቡ ዒምራን ሙሐመድ መኮንን** በሰኔ 2016 E.C በpdf መልኩ ለአንባቢያን ምቹ ሆኖ ቀረበ።



የነብዩላህ ኢብራሂም ታሪክ

[የነብዩላሂ ኢብራሂም ታሪክ ቁርኣን ሳይ ቱክረት ከተሰጣቸው የነብያት ታሪክ ውስጥ በግንባር ቀደምትነት ይመደባል። ታሪካቸው ቁርኣን ውስጥ በ17 ምእራፍ ወደ 69 ጊዜ ተጠቅሷል። ይህ የሚያሳየው ታሪካቸው ምን ያክል እስፈላጊና ቁም ነገር እዘል መሆኑ ነው።]

በኡስታዝ አቡ ዑበይዳህ ባህሩ ተካ በተከታታይ በቴሌግራም ቻናል ቀርቦ

በወንድም አቡ ሚምራን ሙሐመድ መኮንን በለኔ 2016 E.C

በpdf መልኩ ለአንባቢያን ምቾ ሆኖ ቀረበ።